# በስመ አብ ወወልድ ወወመንፈስ ቅዱስ አሐዱ አምላክ አሜን።

## መስከረም 1 -1? ከከከከቀን ፳፻ -2000? ዓ.ም.

# ጥንተ ኧኸምቈ ዘመን

እንደ ኢትዮጵያ ዘመን አቈጣጠር በዘመነ ዮሐንስ የደረስንበ
ትን የ▯▯ -2000? ዓ.ም ዘመን ለማክበር የተሰበሰባችሁ ኢትዮ
ጵያውያን ሆይ ዓመታትን በቸርነቱ እየመገበ የሚያቀዳጅ እግ
ዚአብሔር ይክበር ይመስገንና እንኳን ለዚህ ይጠበቅ ለነበረው
ታሪካዊ የዘመን መለወጫ በዓል አደረሳችሁ አደረሰንዕዕ
መዝ. ፷፬ ፥ ፲፩ -64 ፥ 11?።

የተወደደችውን የጌታን ዓመት እሰብክ ዘንድ ልኮኛልዕዕ
ሉቃስ ፬ ፥ ፲፯ -4 ፥ 17ጠ20?።

በኢትዮጵያና በዓለሙ ዙሪያ የምትኖሩ ወገኖች ሆይ፣

በመግቢያችን ላይ እንደጠቀስነው ሁሉ የሰውን ልጆችና የሚኖሩበትን ዓለም ታሪክ እንጻፍና እናንብብ ብንል ዐባይን በጭልፋ እንዲሉ እንኳንስ በዚህ አጭር ጊዜ ይቅርና የዕድሜ ልክ ጊዜም ቢኖር እንደማይበቃ የታወቀ ነው ። ይሁን እንጂ የአቅማችንን ያህል ግን ረጅሙን በማሳጠር ብዙውን በመቀነስ እንደሚከተለው እናቀርባለን ።

ስለሆነም የ▯▯ -2000? ዓ.ምን ዘመን መነሻ በማድረግ ስለ ኢትዮጵያ ታሪካዊ ህልውና የምንነጋገረው ከጥንተ ፍጥረት ጀምሮ ለመሆኑ በፈጣሪ የተገኘ ሰብአዊ ፍጡር ሁሉ ሊዘነጋው እንደማይገባ አስቀድሞ መታወቅ አለበት።

ይህንንም የምናገኘው የመጀመሪያዋ ትሐቤት፣ የሕግ ምንጭ፣ የታሪክ መዝገብ፣ የጥበብ መሠረት፣ የባህልና የቅርስ ማዕከል የሆነችው ቤተ ክርስቲያን አክብራና ተንከባክባ ከያዘቻቸው ቅዱሳት መጻሕፍት ነው።

የሕግ ምንጭ ከአሰኛት አንዱም ለራሷ ከምትመራበት ፍትሕ መንፈሳዊ ጋር ፍትሕ ሥጋዊ የተባለው ማለትም ሕገ መንግሥት፣ ወንጀለኛ መቅጫና ፍትሐ ብሔር በመባል የታወቀው ሕግና ደንብ ሁሉ ዓለም አቀፍ ሆኖ የተወለደበት በጥቅል ስሙ ፍትሐ ነገሥት የተሰኘው ታላቁ መጽሐፍዋ ነው።

ይህንንም የምታደርገው ፈጣሬ ፍጥረታት እግዚአብሔርን ስለምታመልክና ለእርሱም ስለምትታዘዝ፣ የምትጽፈውና የምትናገረውም ከእርሱ ስለሆነ ለዓለሙና በዓለሙ ላለው ነገር ሁሉ የባለቤትነት ▯ ላፊነት ስለአለባት ነው።

ታዲያ ይህ እንደዚህ መሆኑ ከታወቀ ዘንድ ወደ ተነሣንበት ጉዳይ እንመለስና አስቀድመን እንዳልነው የተወለድንባትን የኢትዮጵያን ታሪክ ስናነሣ የምንጀምረው ከጥንተ ፍጥረት ነው ብለናልና በዚህ መሠረት ቅደም ተከተል ሰጥተን የምናቀርበው።

፩. ዓለምን የፈጠረው ማነውሐ የተፈጠረበትስ ምክንያትሐ
፪. ዓለምና ታሪካዊ ህልውናው ከየት እስከ የትሐ
፫. ኢትዮጵያ ከዓለም ጋር የተካፈለችው የታሪክ ድርሻዋ።
፬. ቤተ ክርስቲያንና ኢትዮጵያዊነት ውለታዋ።
፭. የዓለም ዕድሜ በኢትዮጵያ ኦርቶዶክስ ተዋሕዶ ቤተ ክርስቲያን
አቈጣጠር የሚሉ ነጥቦች ያሉበትን ዝርዝር ነው።

## ፩. ዓለምን የፈጠርው ማነውሐ የተፈጠረበትስ ምክንያትሐ

ዓለምን ፈጥሮ ያስገኘው የፍጥረታት ፈጣሪ እግዚአብሔር ለመሆኑ ሊያጠራጥረን አይገባም። የፈጠረውም ህልውናውን ሊያሳውቅበት፣ ችሎታውን ሊያስደንቅበት፣ ሥልጣኑን ሊያሳይበት፣ ክብሩን ሊገልጽበትና ሊመሰገንበት በተለይም በዋናነት ሊፈጥረው የፈለገውን ሰውን ስለሆነ የተፈጠረው ሁሉ ለእርሱ ነውና በሥጋም በነፍስም ለዚሁ በአርያውና በመልኩ እንደምሳሌው ለፈጠረው ሰው ሊያወርሰውና ይማርበት፣ ይመራመርበት፣ ይፈላሰፍበት፣ ይጠበብበት ዘንድ ለፍላጎቱ አስገዝቶ በላዩ ላይ ሊያሠለጥነው ነው።

## ፪. ዓለምና ታሪካዊ ህልውናው ከየት እስከ የት።

ዓለም በረጅም ጊዜ የዘመናት ጉዞው ያሳለፋችው የሕይወት ታሪኮች ብዙዎቹ ክፉዎች ሲሆኑ ጥቂቶቹ ደግሞ መልካሞች ናቸው። ዘመናቱም በሕግ የተወሰኑና በሦስት የተከፈሉ ሆነው ይገኛሉ። እነርሱም ሕገ ልቡና፣ ሕገ ኦሪት፣ ሕገ ወንጌል የተባሉት ናቸው። ከነዚህ ቅደም ተከተል እንደምናየው

ከነዚህም የመጀመሪያው ሕገ ልቡና፡ የተባለው ሲሆን እርሱም ከአዳም እስከ ሙሴ ያለው ዘመን ነው። ሕገ ልቡናም የተባለው በሥነ ጽሑፍ የተደገፈ ሕግ የሌለው ከመሆኑ የተነሣ በዘመኑ የነበረው ትውልድ ሁሉ የሚያምነው፣ የሚያመልከውና የሚተዳደረው እግዚአብሔር በሕሊናው አድሮ በነገረውና በመራው መሠረት በመሆኑ ነው።

ሁለተኛው ሕገ ኦሪት ነው፡ እርሱም ከሙሴ ጀምሮ እስከ ክርስቶስ ልደት የነበረው ዘመን ነው። ሕገ ኦሪት የተባለውም በሥነ ጽሑፍ የተደገፈ ሕግ፣ ትዕዛዝና ሥርዓት ያለው ሆኖ በዘመኑ ለነበረው ትውልድ ለጥፋቱም ሆነ ለልማቱ በመጠኑም ቢሆን ዳኝነት የሚታይበት ዘመን በመሆኑ ነው።

ከዚህም በስተቀር ሁለቱንም የሕግ ዘመናት በሚያጠቃልል አነጋገር ጥንትነቱን -አሮጌነቱን? በተመለከተ ዘመነ ብሉይ፣ መከራውን -ሥቃዩን? በተመለከተ ደግሞ ዓመተ ኩነኔ -ዓመተ ፍዳ? የሚል ስም ነበረው።

ለምን ቢባል ዘመኑ ቢኖርበት በአካለ ሥጋ ባሪያና ጌታ በሚል ልዩነት የሰው እኩልነት የማይጠበቅበት፣ ከሕጉ መክበድ፣ ከሥርዓቱ መጥበቅ የተነሣ በትንሹም በትልቁም የ□ ጢያአት አይነት ዝቅ ቢል በግርፋት -በእሥራት? ተቀጥቶ፣ ከፍ ቢል በድንጋይ ተወግሮ፣ በእሳት ተቃጥሎ፣ በእንጨት ተሰቅሎ፣ መርዝ ጠጥቶ ምሕረት በሌለው አሰቃቂ ሞት የሚገደልበት፣

በተፈጥሮም ሆነ በበሽታ አካል የጎደለው ሁሉ ፈውስ እስከ አላገኘ ድረስ፣ በተለይም የሔዋን ስሕተትና እርግማን እየተጠቀሰ በሴቶች ላይ የሚታየው ወር□ዊ ልማድና አራስነታቸው በተሰጠው የራሱ የሆነ የጊዜ ገደብ እስካላነፃቸው ድረስ እንደ ርኩስ ነገር ተቆጥሮ ከሰው የሚገለሉበት፣

ምን ይህ ብቻ ሰውም ሆነ እንስሳ ከሞተ በኋላ በድኑን የነካ፣ ርኩሳን ናቸው ተብለው የማይበሉትን እንስሳትና ምንም ቅዱስ ቢሆን እነርሱ የነከሱትን ሁሉ ፀጉር ሳያበቅል እንኳን የበላ የዳሰሰ ፈ ስንቱ ተነግሮ አልቆ እንዲያው በጥቅሉ ይህንም ሆነ የመሳሰለውን ሁሉ በመተላለፍ የተሳሳተ እንደዚሁ ርኩስ ነው የሚባልበት፣

ቢሞቱ ደግሞ በአካለ ነፍስ ምንም በጎ ሥራ ቢሠራ የተሰጠው ተስፋ ድኅነት ደርሶ እስኪፈጸም ድረስ የጽድቅ ዋጋ የማይገኝበትና ለዲያቢሎስና ለአጋንንቱ አልፎ ተሰጥቶ በእሳተ ሲያል የሚቃጠሉበት ፍጹም የሆነ የጨለማ ዘመን ሆኖ በመገኘቱ ነው።

ሦስተኛው <u>ሕገ ወንጌል የተባለው ነው</u>፡ እርሱም እስከ አሁን ያለውና ወደፊትም እስከ ዓለም ፍጻሜ ድረስ ለመጨረሻ ጊዜ ጸንቶ የሚኖረው ዘመነ ሐዲስ ነው። ሕገ ወንጌል የተባለውም ወንጌል ማለት የምሥራች ማለት ነውና፣ በአዳምና በሔዋን ስሕተት -በደል? ምክንያት ለ□ □ □ □ -5500? ዘመን በእሳተ ሲያል ሲቀጣ የኖረው ትውልድ ከመርገመ ሥጋ ከመርገመ ነፍስ ተላቆ፣ በድኅነተ ሥጋ ድኅነተ ነፍስን፣ በበረከተ ሥጋ በረከተ ነፍስን በማግኘት የዘላለም ነፃነትን የተጎናፀፈበት፣ አዳኝ መድ□ኒት በሆነው በመድ□ኄዓለም ክርስቶስ ምሕረት ቸርነት ሰጪነት፣ ርኅራኄና ይቅርታ አድራጊነት የመከራ ጨለማው ተገፎለት የሕይወት ብርሃንን ያሳየበት ዘመን በመሆኑ ነው።

ለዚህም ነው ነቢየ እግዚአብሔር ኢሳይያስ በማቴዎስ ፬ ÷ ፲፪»ጠ ፲፯ -4 ÷ 12 ጠ 17? ለተፈጸመው ተስፋ አስቀድሞ በም ፱÷ ፪ ጠ ፫ -9 ÷ 2 ጠ 3? ላይ በጨለማ የሄደ ሕዝብ ብርሃን አየ፣ በሞት ጥላ አገርም ለኖሩ እንዲሁ ብርሃን ወጣላቸው ሲል የተነበየው።

ታዲያ እነዚህ የሕግጋት ዘመናት ምን እንደሚመስሉ በምሳሌ እንረዳ ብንል **የሕገ ልቡና ዘመናት ከማታ እስከ መንፈቀ ሌሊት እንዳለ ጥቅጥቅ ጨለማ፣ የሕገ ኦሪት ዘመናት ደግሞ ከመንፈቀ ሌሊት እስከ ንጋት እንዳለ ጊዜ ሲሆኑ፣ የሕገ ወንጌል ዘመናት ግን ከንጋት ጀምሮ እንዳለ ሙሉ ቀን ሆነው ነው የምናገኛቸው። ይህም በአጭሩ ሲተረጎም ተስፋ የጨለመባቸው፣ የተስፋ ጭላንጭል የታየባቸው፣ ተስፋው የተፈፀመባቸው ዘመናት ማለት ይሆናል።**

<u>፫. ኢትዮጵያ ከዓለም ጋር የተካፈለችው የታሪክ ድርሻዋ</u>

ኢትዮጵያ ከዓለም ጋር የተካፈለቻቸው የታሪክ ድርሻዎቿ ሁለት ዓይነት ናቸው። እነርሱም ሃይማኖታዊና፣ መንግሥታዊ የሆነት የሕዝበ እግዚአብሔር ማሕበራዊ ኑሮዎች ናቸው። ለዚህም የታሪክ መዝጋቢዋ ቤተክርስቲያን እንደሆነች የታወቀ ነው። እንዴት ቢባል ከታሪካውያን ሕንጻዎችዋ ጀምሮ በስነ ጽሑፍ፣ በሥዕል በቅርጻ ቅርጽ መዝግባና በቅርስ መልክ ጠብቃ የምትገኘውና የምትነበኘው እርስዋ ነችና። ይህም ብቻ አይደለም ለአምልኮተ እግዚአብሔር የምትገለገልባቸው ጥንታውያን ንዋየ ቅድሳትዋም ታሪክ አስመዝጋቢዎች ናቸው።

የታሪክ ድርሻዋን በተመለከተም ጥንታዉያን ከሚባሉት አገሮች አንድዋና ዋናዋ እንደመሆንዋ መጠን በቅድሚያ ሃይማኖትዋን የተቀበለችው ከጥፋት ውሀ በኋላ ወደ ኢትዮጵያ የመጣውና የኖኅ ልጅ የሆነው የካም ዘር ኩሽ ስለሆነ፣ ከዚያም ከልደተ ክርስቶስ በፊት በ▯▯▯ -1900? ቀጥሎም በሰሎሞን ዘመነ መንግሥት በ▯▯ -1000? ዓ.ዓለም ከታቦተ ጽዮን ጋር የገባው አሁንም ያው የኖኅ ልጅ የሆነው የሴም ዘር ስለነበር ሁሉም የገቡት ማለትም የመጀመሪያዎቹ፣ የመምለኬ እግዚአብሔር ኖኅን የሕገ ልቡና፣ የኋለኞቹ የብእሴ እግዚአብሔር ሙሴን የሕገ ኦሪት እምነታቸውን ይዘው ነውና ከዚህ ጊዜ ጀምሮ ነው።

ከዚህ ጋር በተያያዘ መልኩ ሕገ ወንጌልን ስትቀበልም ከመጀመሪያዎቹ አንዷ የሆነች ቀዳማዊት ናት። እንዴት ቢባል ክርስትና ወደ ኢትዮጵያ የገባውና የተመሠረተው በሐ. ሥራ ፰ ÷ ፳፮ ጠ ፵ -8 ÷ 26 ጠ 40? ላይ እንደ ተጻፈው ከልደተ ክርስቶስ በኋላ በ ፴፬ -34? ዓ.ም ነው። ተምሮ ተጠምቆና ተቀብሎ ያመጣው የመጀመሪያው ክርስቲያንም ህንደኬ የተባለች የኢትዮጵያ ንግሥት አዛዥና ጃንደረባ የሆነው የኢየሩሳሌም ተሳላሚ ነው። ያመጣውም ፊልጶስ ከተባለው ሐዋርያ ተቀብሎ ነው። የተስፋፋው ግን ለመጀመሪያ ጊዜ የኢትዮጵያ ጳጳስ በሆነው ሶርያዊ በአቡነ ሰላማ ከሣቴ ብርሃን ነው። ይህም ብቻ አይደለም የኢትዮጵያ ኦርቶዶክስ ተዋሕዶ ቤተ ክረስቲያን ታሪክ በሚለው የብፁዕ አቡነ ጎርጎርዮስ መጽሐፍ ላይ እንደተተረከውም

- *ሩፊኖስ፣ ቴዎዶይሪጦስ፣ ሶቅራጥስ፣ ሶዞሜኖስ የተባሉት የታሪክ ጸሐፊዎች እንደመዘገቡት ማቴዎስ የተባለው ሐዋርያ ኢትዮጵያ ገብቶ አስተምሯል ብለዋል።*

- *ከ▯▯▯▯ ጠ ፫፻፲፱ -317 ጠ 419? ዓ.ም የነበረውና ጀሮም -ኢየሮኒሞስ? የተባለው የላቲን ቤተ ክርስቲያን አባትም የኢትዮጵያ ሐዋርያ ቅዱስ እንድርያስ ነው ብሏል።*

- *ዮሐንስ አፈወርቅ የተባለው ታላቁ የቤተ ክርስቲያን ሊቅና ሊቀ ጳጳስም ለኢትዮጵያ የመጀመሪያው ሐዋርያ ቅዱስ ቶማስ ነው ብሏል።*

እዚህ ላይ ሁሉንም ስለ ኢትዮጵያ ይህን ያህል ያነጋገራቸው ኢትዮጵያ ከጊዜ በኋላ ኋላ ቀር ከሚባሉት የአፍሪቃ አህጉር አንዷ ነች ብትባልም በመጽሐፍ ቅዱስ ግን ከመጀመረያው አንሥቶ የተመዘገበችና ለእምነትዋ ብዙ ሥፍራ ያላት ባለ ታሪክ አገር ከመሆንዋም በላይ በተለይም በሃይማኖት የሚመስሉንም ሆኑ የማይመስሉን ሁሉ የሃገራቸው መንግሥት አረመኔ -አሕዛብ? ሆኖና አላስቀምጥ ብሎ ሲያሳድዳቸው ኢትዮጵያ የምትባል እንግዳ ተቀባይና አክባሪ የሃይማኖትና የሰላም አገር አለች ብለው በመምጣት ተከብረውና ተወድደው በፍቅር አንድነት የሚኖሩበት አገር ሆና ስለአገኟት ነው።

ከዓለም ጋር ተካፈለችው ያልነው ሌላው ደግሞ መንግሥታዊ አመሠራረትን ሕዝባዊ አደረጃጀትን፣ ታሪካዊ አመዘጋገብን፣ ባህልን፣ ስልጣኔን፣ የድል ▯ ይልን፣ የነፃነት ክብርን፣ ወኔንና ጀግንነትን፣ ሰላም ወዳድነትንና ታማኝነትን፣ ዳኝነትን፣ ፍትሕ ርትዕናን የመሳሰለውን ነው።

በዚህም ከታወቁት አገሮች ሁሉ አንድዋና ዋናዋ ነበረች፣ አሁን ግን ነበር ነው እንጂ ከተባለው ሁሉ የምናየው ምንም ነገር የለም። ቢኖርም ስትካፈለው የምናየው በሁሉም ነገር ተራቁታ ከድ▯ ነት ላይ ስለ ወደቀች እየተመጸወተች የምታመርተውንና ከእጅ ወደ አፍ የሆነውን ንበረትዋን የምታወድምበት ጦር መሣሪያ ብቻ ነው።

ለዚህም ያበቃት ከጥንት ጀምሮ የአብዛኛዎቹ የመሪዎችዋ በጦርነት ላይ መመሥረትና ደም እያፈሰሱ መፈራረቅ፣ ሕዝብዋን ከማሠልጠን፣ አገሪቱን ከማልማትና ከማበልጸግ ይልቅ በራስ ወዳድነታቸው ራሳቸውን ብቻ አንግሠውና አስከብረው፣ ሌላውን አምሰው አተራምሰው እንዲሁም እርስ በርሱ በጦርነት እንዲተላለቅ አድርገው መኖራቸው ነው።

ይህም እውነት ነው እንጂ ባይሆንማ ኑሮ ኢትዮጵያን የመሰለ አየረ ጥሩ፣ ጠባየ ኩሩ፣ አብሮ የመመገብ ማሕበራዊ ኑሮ ያላት፣ የሃይማኖትና የግብረ ገብ አገር የት ይገኝ ነበርሐ ከዚህ ሁኔታዋ ጋርስ እንደ አጀማመሯ ሰላም አግኝታ ብትቀጥል ኑሮ ዛሬ በዚህ በሠለጠነው ዓለም መካከል የት ትደርስ ነበርሐ አዬ እስኪ ለሁሉም ወደ እግዚአብሔር የዘረጋችው እጅዋ ሳይታጠፍ ምሕረቱን ያወርድላት፣ ሰውም ይስጣትዐዐ

<u>፩. ቤተ ክርስቲያንና ኢትዮጵያዊነት ውለታዋዐዐ</u>

ቤተ ክርስቲያን የምትመራበትና አምልኮተ እግዚአብሔርን የምትገልጽበት ሕንፃ መቅደሷ፣ ቅዱሳት መጻሕፍቷና ጠቅላላ ንዋየ ቅድሳቷ ሁሉ ሰማያዊ ከሆነው ዘላለማዊ የጽድቅ ትምህርት ሰጭነቱና የበጎ መንገድ መሪነቱ ሌላ ለጊዜው በዚች ጊዜያዊነት ዓለም እስከ አለን ድረስ ለኢትዮጵያ የታሪክ ማንነትና ምንነት ሁለንተናዊ መዝገብ ለመሆኑ በሀገር ውስጥ በሚነሱም ሆነ ከሀገር ውጭ ለጉብኝት በሚመጡ የታሪክ መዝጋቢዎችና ተመራማሪዎች ዘንድ የተረጋገጠ ነውዐዐ

እንዴት ቢባል ለመጀመሪያ ጊዜ የስነ ጽሑፍ መሥራች የነበረው፣ የአዳም ሰባተኛ ትውልድ የሆነውና እስከነ ሕይወቱ የተሰወረው የእግዚአብሔር ሰው ሄኖክ ሲሆን ከጊዜ በኋላ ደግሞ ያጠናከረውና ያስፋፋው ነቢየ እግዚአብሔር ሊቀ ነቢያት ሙሴ ስለነበረ ነውዐዐ

ቤተ ክርስቲያን በስነ ጽሑፍ መሥራችነትና፣ በታሪክ መዝጋቢነት የመጀመሪያ ናት ያልነውም ወደ ኢትዮጵያ መጥቶ አሁን በአክሱም ቤተ ክርስቲያን ውስጥ የሚገኘውና የዓለም ታሪክ ጸሐፊዎችን እያመራመረ የሚያነጋግረው ያው ሙሴ ከእግዚአብሔር አግኝቶ -ተሰጥቶት? የቀረጸውና እላዩ ላይ ስመ እግዚአብሔር፣ የሕግና የትዕዛዝ መመሪያ ከሥርዓቱ ጋር የጻፈበት ጽላተ ሕግ ከማስረጃዋቹ ሁሉ አንዱ በመሆኑ ነውዐዐ

እነሆ ከዚያን ጊዜ ጀምሮም ነው ቤተ ክርስቲያን ከመንፈሳዊው ቀጣይ ታሪኳ ጋር የደጎቹንም የክፉዎቹንም ታሪክ በቅርጻ ቅርጽና በስነ ጽሑፍ መዝግባ፣ በቅርስ መልክ ጠብቃ ለተመልካቾችና ለተራኪዎች እያቀረበች ነበርን የምታስነብበው።

ለዚህም ነው ብፁዕ አቡነ ጎርጎሪዮስ ይባሉ የነበሩ ሊቀ ጳጳስ አስቀድመን በጠቀስነው መጽሐፋቸው ስለ ኢትዮጵያና ስለ ቤተ ክርስቲያን ሊተርኩ ሲጀምሩ በመቅድማቸው ማጠቃለያ ላይ የኢትዮጵያ ኦርቶዶክስ ተዋሕዶ ቤተ ክርስቲያን ለኢትዮጵያ ሕዝብ ያበረከተቻቸው ስጦታዎች ብዙ ሲሆኑ ከእነዚህም ውስጥ

ሀ. ሙሉ ትምህርት ከነስጦታው
ለ. ፍጹም ቋንቋ ከነፊደሉ
ሐ. ስነ ጽሑፍ ከነጠባዩና ከነሞያው
መ. ኪነ ጥበብ በየዓይነቱ

ሰ. ስነ ጥበብ በየመልኩ
ረ. ጥንታዊ ቅርስ ከነ ታሪኩ
ሰ. እምነት ከነፍልስፍናው
ሸ. ነፃነት ከነክብሩ
ቀ. አንድነት ከነጀግንነቱ
በ. አገር ከነድንበሩ ከነፍቅሩ
ተ. ስም ከነምልክቱ -ከነትርጉሙ? ናቸው ያሉትዕዕ

ይህም ብቻ አይደለም ቤተ ክርስቲያን ለኢትዮጵያ ያላት ከፍተኛ ውለታ፣ ጠላት ባሕር ተሻግሮ ደንበር ደፍሮ በመግባት ሀገሪቱን ያለሀገሩ ሀገር ሊያደርግ፣ ዜጋዎቿን በገዛ ርስተ ምድራቸው ስደተኛ አድርጎ ሊያሠቃይ፣ ሃይማኖታቸውን ሊያስክድ፣ ባህላቸውንና ታሪካቸውን ሊያጠፋና ቅርሳቸውን ሊዘርፍ በመጣበት ጊዜ ግንባር ቀደም ሆኖ በመዝመትና ትውልዱ ጀግንነትን፣ አገር ወዳድነትን ለሃይማኖት፣ ለታሪክና ለባህል ተቆርቋሪነትን ይዞ እንዲሰለፍ በማስተማርና በማበረታታት፣ ፊርቶ ወደ ላ የሚለውን ደግሞ በማውገዝ በየጊዜው የታገለችና መሥዋዕትነት ከመክፈል ጋር ድል ነሥታ ነፃነትን ያስረከበች፣ የገዛ ልጆቿ ሲጣሉ ግን አንተም ተው አንተም ተው ከማለት ጋር ሰይፋችሁን ወደ አፎቱ ሠራዊታችሁን ወደ ቤቱ መልሱ እያለች የምታስታርቅ የይቅር ባዩ እግዚአብሔር የይቅርታ ቤት መሆኗም የታወቀ በታሪክም የተመዘገበ ነውዕዕ

እዚህም ላይ በከፍተኛ አድናቆትና በዋናነት የምንተርካቸው ማለትም ለሃይማኖታቸውና ለሀገራቸው ሲሉ መሥዋዕትነት ከፍለው ያለፉ ቢኖሩ በአዲስ አበባ አቡነ ጴጥሮስ በኤሉባቦር አቡነ ሚካኤል የተባሉት ሊቃነ ጳጳሳት መሆናቸው መረሳት የሌለበት መሆኑን ነው።

**ይህም በመሆኑ ቤተ ክርስቲያን የኢትዮጵያ አካለ ነፍስ እንዲሁም ደግሞ ኢትዮጵያ የቤተ ክርስቲያን አካለ ሥጋ ተብለው በውሕደት አካል ቢታዩ ቅር የሚያሰኝ አይመስለኝምዕዕ እንዴት ቢባል ከዚህ በላይ ከረጅሙ በአጭሩ ለተዘረዘረውና በየታሪክ መዝጋቢው መጽሐፍ ላይ ተጽፎ ለተነበበው ሁሉ *አእምሮ ልቡና ሆና ያለመርሳትና ያለመዘንጋት በዓለም የታሪክ መዝገብ ያስመዘገበቻት፣ አንደበት ሆና ታሪኳን እያነበበችና ማንነቷን የሚገልጸውን መጽሐፍ፣ ቅርጻቅርጽ፣ ሥዕልና የመሳሰለውን መግለጫዋን እያስመረመረች ያስተረከቻት፣ ትንፋሿ ሆና ለታሪካዊነት ትበቃ ዘንድ ለታሪክ የሚያበቃ ሕይወት ስጠታ ያንቀሳቀሰቻት በመሆንዋ ነውዕዕ***

<u>፭. የዓለም ዕድሜ በኢትዮጵያ ኦርቶዶክስ ተዋሕዶ ቤተ ክርስቲያን አቈጣጠር</u>

በኢትዮጵያና በጥንቱ የዓለም አብያተ ክርስቲያናት ዘመን አቈጣጠር ዓለም ከተፈጠረበት ጊዜ ጀምሮ እስከዚሁ ዘመን ድረስ ጠቅላላ ዕድሜው ፯፼፭፻ -7500? ዓመተ ዓለም ነው። ከዚህ ውስጥ ግን ከአዳም እስከ ልደተ ክርስቶስ የነበረው ፭፼፭፻ -5500? ዓመተ ኩነኔ ሲሆን ከልደተ ክርስቶስ እስከዚሁ ዘመን -ዓመት? ድረስ ያለው ደግሞ ፪፼ -2000? ዓመተ ምሕረት ሆኖ የሚገኘው ማለትም ለዚህ ላደረሰን ለእግዚአብሔር ክብር ምስጋና ይግባውና ይኸው የደረስንበት ዘመን ነው።

እዚህ ላይ ስለዚች ዓለም ዕድሜና ህልውና ስናነሣ በተለያዩ መንፈሳውያንና ዓለማውያን ተመራማሪዎች ልሳን ብዙ የተለያዩ አባባሎች እንዳሉ መዘንጋት የለብንም።

እነሱም በቅድሚያ በዓለማውያኑ ተመራማሪዎች ብንጀምር አንዳንዶቹ በብዙ ቢሊዮን የሚቈጠር ዕድሜ እንዳላት ወስነው ሲናገሩ ሌሎቹ ደግሞ ጥንትም የነበረች ናት ወደፊትም አታልፍም ብለው ግምታቸውን ሲያረጋግጡ የምንሰማቸው ናቸው ። የሚመራመሩትም በሰው ሰራሽ ነገሮችና በተፈጥሮ ክሥተቶች ማለትም በቅሬተ አፅጽምት በቋጥኞችና በመሳሰሉት እየተፈላሰፉ በሒሳብ ስሌት አገኘነው በሚሉትና በመሳሰለው መላምት ነው። የምርምራቸው ውጤትም የተረጋገጠና ከመጨረሻ ውሳኔ ላይ የደረሰ አይደለም። ምክንያቱም አዳዲስ ፈላስፋዎች -ተመራማሪዎች? በተነሡ፣ ካለፈው የምርምር ውጤት ተነሥተው የራሳቸውን አዲስ ምርምር በጀመሩና በቀጠሉ፣ ከዚያም አዳዲስ ክስተቶችን በአገኙ ቁጥር እንደራሳቸው መላምት ውሳኔያዊ ማረጋገጫቸው ተመሳሳይነቱን ጠብቆ ስለማይገኝ ነው።

እንዲህም የሚሆንባቸው ከፊሎቹ ለስነ ፍጥረቱ ሁሉ ፈጣሪ አለው ብለው ካለማመናቸው የተነሣ የምርምር መነሻቸውን ከፈጣሬ ፍጥረታት እግዚአብሔር ስለማይጀምሩ ሲሆን፣ ከፊሎቹ ደግሞ በፈጣሪ መኖር ቢያምኑም እንኳን ከመንፈሳውያኑ መጻሕፍት ይልቅ ፍልስፍናዊ ምርመራቸው ስለሚበልጥባቸው ነው። ሌላው ደግሞ የሃይማኖት ሰዎች ነን በምንለው አማንያን በኩል እስከ ጊዜያችን ያለው የዘመን አቈጣጠር ነው። እርሱም ለሁሉም መነሻው ዕድሜ ወስኖ ዘመን መጥኖ የሚያስረዳውና የሚያረጋግጠው ቅድስ መጽሐፍ እንደመሆኑ የስነፍጥረታት አጀማመሩ አንድ ዓይነት ሲሆን የልደተ ክርስቶስን ዘመን አካባቢ አስመልክቶ ያለው አጨራረሱና አደራረሱ ግን እንደየእምነቱ፣ እንደየአገሩ ታሪክና ባህል የተለያየ ሆኖ ነው የምናገኘው።

ይህም የሆነው አንዱ በቀና መንፈስ በጀመረው ላይ ምን አልባት የጎደለ ቢኖር እንደዚሁ ሌላው ቅንነትና ትሕትና ባለው መንፈስ ተነሣስቶ ማሟላት ሲገባ ከእርሱ ይልቅ እኔ እበልጣለሁ በሚል መንፈስ ዝናን ለማትረፍና አዋቂም ለመባል ያህል ከተቃውሞ ጋር የቅመራ ትክክልነቱን እንዲያጣ በማድረግና በመሳሰለው ነው።

ለዚህም ነው እስከ ፩፲፭፻፹፪ -1582? ዓ.ም ድረስ በዓለም አቀፍ ደረጃ አንድ አይነት ቀመረ ዘመን ሆኖ ከቆየ በኋላ ተለውጦ አሁን ያለውን የዘመን አንድነታችንን ያናጋው። ከጊዜ በኋላ ያፋለሱት አሸንፈው ትክክለኛ የሆንነው ተሸንፈንና ብቻችን ቀርተን የምንታየውም ሀብትና ድህነት በፈጠረው ልዩነት እንጂ ዕውቀት አንሶብን እውነት ጠፍቶብን አልነበረም።

ከዚህ ጊዜ ጀምሮ ግን እንደነበረው መቀጠል አልቻለም። ይኸውም አሁን እንዳልነው በዚህ ዘመን በተነሣው፣ የሮም ቤተ ክርስቲያን 13ኛ -ፓፓ? በነበረውና ጎርጎርዮስ በተባለው አማካይነት ቀደም ሲል የነበረው ዓለም አቀፍ የዘመን አቈጣጠር መሥመሩን ለቆ አከራካሪ ነገርን በመፍጠሩ ነው። ለዚህም አከራካሪ መነሻ የሆነው ወደፊት እንደምንገልጸው ተመራምሬ አገኘሁት ያለውን ቀመር ዘመን ተጠቅሞ 7-8? ዓመት ወደኋላ ቀርተናል የሚለውን ምክንያት አድርጎ ነው።

እዚህ ላይ ቅድሚያ የምንሰጠው አንድ ዐቢይ ነገር አለ። እርሱም የዘመን አቆጣጠር እንዴት ተጀመረሕ ያስፈለገበትስ ምክንያት ለምን ይሆንሕ አካሄዱስ፣ አገሳገሱስ እንዴት ነበርሕ አሁንስ ከምን ላይ ደርሶ ይገኛልሕ የሚለውንና የመሳሰለውን ነው። ይህንም ቅደም ተከተል ሰጥተን ስንመለከተው የምናገኘው መልስ

፩. የዘመን አቆጣጠር የተጀመረበትና ያስፈለገበት ዋናው ምክንያት የሰው ልጅ በዓለም ላይ እስካለ ድረስ የኑሮ ምልልሱ ከሌሎች ስነ ፍጥረታት የተለየና ከልቡ ሐሳብ አመንጭቶ የመወሰን፣ በአንደበቱ የመናገር ባሕርያዊና አእመሮአዊ ጠባይ ስለአለው

በአጭሩ የሚያደርገውን መንፈሳዊና ዓለማዊ ነገር ሁሉ በግልም ሆነ በማሕበራዊ ኑሮ በደቂቃና በሰዓት፣ በመዓልትና በሌሊት፣ በሳምንትና በወር፣ በወቅትና በዓመት የአጭርና የረጅም ጊዜ ዕቅድ እያወጣ የሚመራበት መርሐ ግብር የሚያስፈልገው ሆኖ በመገኘቱ ነው።

ለምሳሌ ያህል ሃይማኖታዊና ሕዝባዊ በዓላትን ለማክበር የእርሻ የንግድና የመሳሰሉትን ተግባራት ሁሉ በየወቅቶቹ ካለው የአየር ጠባይ ጋር እያስማሙና እየተስማሙ ለመሥራት በአጠቃላይም የጊዜውን በጊዜው የወቅቱን በወቅቱ እየከፋፈሉና ከአቅም ጋር እያቻቻሉ በስነሥርዓት ለማራመድና ለማከናወን እንዲመች ለማድረግ ስለሚጠቅም ነው።

፪. የጀመሩትን ተመራማሪዎች በተመለከተ እነማን እንደነበሩ መጻሕፍቱ ያስረዱን በተለያዩ አገሮች የተለያዩ ተመራማሪዎች መሆናቸውን ነው እነሱም አይሁዳውያን፣ ግብፃውያን፣ ሮማውያን፣ ግሪካውያንና የመሳሰሉት ተመራማሪዎች እንደሆኑ ነው ያወቅናቸው።

፫. መመራመሪያ የሚያደርጓቸውን የፀሐይን መዓልታዊ የጨረቃን ሌሊታዊ ዑደት -ዙረት? በሰከንድ እየጠቃቀሉ፣ በደቂቃ እያጎሉ ሰዓት ላይ በማድረስና ዕለታትን -ቀናትን? በማስገኘት ከዚያም ወደ ሳምንት ወደ ወርና ወደ ወቅት አሳድጎ በዓመት ዓመታትን በዘመን ዘመናትን በማስገኘትና በማስቈጠር ነው።

ይህም ሲሆን እንደተመራማሪነታቸው አገኘነው የሚሉት ፀሐይ በየወሩ የምትሰጠውን ያልተጓደለ የ -30? ቀን ብርሃን፣ ጨረቃ ደግሞ በሁለት ወር ውስጥ አንድ ጊዜ ስለምትጠፋ በዚህ ጊዜዋ መካከል የምትሰጠውን የ -፳፱? እና የ -፴? ቀን የብርሃን ዑደት -ዙረት? እያባዙና እየደመሩ በማካፈል ነው።

፬. የዘመን አቆጣጠራቸውን በተመለከተ መነሻቸውን የሚያደርጉት

- አይሁድ የስነ ፍጥረትን ጥንተ ዘመን በማሰብ ከመጀመሪያው።
- ግሪኮች ደግሞ የኦሎምፒክ ዓመታዊ ውድድራቸውን ከአደረጉበት ከልደተ ክርስቶስ በፊት በ -776? ዓመተ ዓለም።
- ሮማውያንም እንዲሁ በንጉሣቸው በሮምሎስ ጊዜ ከተማቸው ሮም ከተመሠረተችበት ከክርስቶስ ልደት በፊት በ -753? ዓመተ ዓለም።
- የጥንት ግብፃውያን እንደሌሎቹ የታሪክ መነሻ ሳይኖራቸው ከጥንት ጀምሮ እያንዳንዳቸው በ -30? ቀናት በተከፈሉ 12 ወሮችና በ5 ተጨማሪ ቀናት በተጠቃለሉ ፫፻፷፭ -365? ቀናት ዓመታትን በመቈጠር።
- ከጊዜ በኋላ የተነሡ የኦርቶዶክስ ተዋሕዶ ግብፃውያን ደግሞ በዲዮቅልጥያኖስ ዘመነ መንግሥት የተፈጁት ክርስቲያኖች ሰማዕታት በሚታሰቡበት ከክርስቶስ ልደት በኋላ በ -284? ዓ.ም ነው። ይህም በመሆኑ ሁሉም በየበኩላቸው የዘመናቸውን መነሻ የዓመታቸውን መጀመሪያ የሚቈጥሩት በዚህ ዓይነት ነበር።

ይህ በዚህ እንዳለ በ -532? ዓ.ም ግን በሮም ከተማ ይኖር በነበረውና ዲዮናስዮስ ኤክስጁስ በተባለው መነኩሴ የቀመረ ዘመን አቈጣጠር ከሰው ታሪክ መጀመሩ ቀርቶ ከክርስቶስ ልደት ጀምሮ እንዲሆን ተደረገ።

ወገኖቻችን እዚህ ላይ የምናሳስባችሁ ነገር ቢኖር ወደ ስነ ጽሑፋችን መጨረሻ አካባቢ የምንጠቁማችሁን የባሕረ ሐሳብ -የዘመን መቁጠሪያ? መጻሕፍትን አንብባችሁ ሲከብዳችሁም የሚመለከታቸውን መምህራን ጠይቃችሁ እንድትረዱ ካልሆነ በቀር በዚህ አጭር ጊዜ ውስጥ ሁሉንም ዘርዝረን ለመግለጽና ለማስረዳት ስለማንችል ለአሁኑ ያህል ግን በኢትዮጵያውያንና በአውሮፓውያን መካከል ጎልቶ ወደሚታየው የዘመን አቈጣጠር ልዩነት ረጅሙን አሳጥረን ብዙውን ቀንሰን የምናመራችሁ መሆኑን እንድታውቁልን ነው።

ይህንን በዚህ ከተስማማን የሚቀጥለው እንዲህ ነበር። እያነጋገረን በመጣው ታሪካዊ አገላለጻችን መሠረት የነበረው ይኸው የዘመን አቈጣጠር ልዩነት ጠፍቶ አንድ የሆነው ማለትም ከአውሮፓውያንና ከግብፃውያን ጋር ያለው የኢትዮጵያ ዘመን አቈጣጠር እስከተለያየበት እስከ ጎርጎርዮሳዊው ዘመን አቈጣጠር ድረስ የሮማው ዩሊዮስ በነገሠ ጊዜ የሮማውያን ዘመን አቈጣጠራቸው ትክክል አለመሆኑን በመረዳት ከክርስቶስ ልደት በፊት በ46 ዓመት ሶሲጂነስ የተባለውን ግብፃዊ የከዋክብት ምሁር አቈጣጠሩን እንዲያሻሽል አዘዘው።

ሶሲጂነስም የፀሐይንና የጨረቃን አቈጣጠር አስተካክሎ በቅድሚያ የፀሐይን አቈጣጠር በተመለከተ በየአራት ዓመቱ አንድ ጊዜ ሠግር -የቀን መጨመር ሽግግር? እንዲኖርና የሦስቱ ዓመት ፫፻፷፭ -365? ቀን እየሆነ ሲፈራረቅ የአራተኛው ዓመት ግን ፫፻፷፮ -366? ቀን እንዲሆን ወሰነ።

የጨረቃን አቈጣጠር በተመለከተ ደግሞ ሚቶን የተባለውን የግሪክ ፈላስፋ አሠራር በማረም የጨረቃን ቀኖች አዲስ ከተነሡት ሁኔታዎች ጋር እንዲስማማ አደረገ የዓመቱንም አከፋፈል እንደ ግሪኮች ሳይሆን እንደ ሮማውያን አደረገው። በዚህን ጊዜ በሶሲጂንስ ምክር መሠረት ዩልዮስ ቄሣር ሕዝብ ሁሉ የጨረቃን አቈጣጠር እንዲያቆም ትእዛዝ አስተላለፈ።

በእርግጥ ሶሲጂነስ ለዩልዮስ ቄሣር ያዘጋጀለት የዘመን አቈጣጠር ከቀድሞ ግብፆች አቈጣጠር ጋር ይቀራረባል ይህም የሆነው ፲፪ -12? የቀድሞ ግብፆች ወሮች ሁሉም 30 ቀኖች ያሏቸው ሲሆኑ ፲፪ -12? የሮማውያን ወሮች ግን ፴ -30?ከ ፴፩ -31?ከ ፳፰ -28?እና ፳፱ -29? ቀኖች ያሏቸው ሆነው ነው የሚገኙት።

በዚህ ዓይነቱ አቈጣጠራቸውም የዓመቱ ቀኖች በዩሊዮሳዊውም ሆነ በግብፆች አሠራር 365 ወይም በአራት ዓመት አንድ ጊዜ 366 ቀኖች ሆነው ነው የተቀመሩት። ይሁን እንጂ በመጠኑም ቢሆን ልዩነት አለው። ይኸውም ግብፆች ዓመቱን ለመሙላት ፭ -5? ወይም ፮ -6? ቀኖች ያሏት 13ኛ ትንሽ ወር ስትኖራቸው ሮማውያን ግን አስቀድመን እንደጠቀስነው ፫፻፷፭ -365? ወይም ፫፻፷፮ -366? ቀኖችን በ□□ -12? ወሮች ውስጥ ሲያጠቃልሏቸው ነው የሚታዩት።

በመጠኑም ቢሆን ያልንበትንም ምክንያት ምንም ቢያከራክርና ወጥ የሆነ ወር□ዊ አቈጣጠር የሌለውና ከፍና ዝቅ ያለ ሆኖ ቢያደናግርም እስከዚህም ድረስ ልዩነቱ ሰፍቶ የዓመተ ምሕረትን መዛባት አለማስከተሉን በማየት ነው። ልዩነት ፈጥሮ ክርክር ያስከተለውና ተከታዩን ትውልድ ግራ ያጋባው ስንለው እንደመጣነው ይኸው ከክርስቶስ ልደት በ□ላ በ□□ □□□ □ -1582? ዓ.ም የተነሣው ጎርጎርዮስ የተባለው 13ኛ የሮም ቤተ ክርስቲያን ፓፓ አስተካከልኩ ብሎ እንደመሰለው የቀመረው የዘመን አቈጣጠር ነው።

አቈጣጠሩንም የፈጠረው የዩልዮስ ቄሣር ዘመን አቈጣጠር ከትክክለኛው ዘመን አቈጣጠር ልዩነት አለው። ልዩነቱም ዓመቱ በሙሉ በ□□□□ -365? ቀኖችና በ□

-6? ሰዓቶች የተወሰነ በመሆኑ ነው። ይህንንም ለማወቅ የተቻለው የሃይማኖት በዓላት የሚከበሩባቸው ጊዜያት ከወቅታቸው ቀድመው ሲመጡ በመገኘታቸው ነው። ስለዚህም ለዘመኑ አቈጣጠር እርማት ያስፈልገዋል ብሎ በመነሣት ነው።

ይህንንም ብሎ አልቀረም ዓሥራት ገሐማርያምና ገብረ ሕይወት መሐሪ የኢትዮጵያና የአውሮፓ አቈጣጠር ለምን ተለያየ በሚል ርእስ በ□□□□ □ -1987? ዓ.ም በጻፉት መጽሐፍ ላይ እንደተጠቀሰው እንዲረዱት ባለሙያዎች ናቸው የሚላቸውን ሁለት ሰዎችን መረጠ እነርሱም ካልቪዮስ የተባለው ጀዝዊታዊና አልዮስዩስ የተባለው ሐኪም ናቸው። ባለሙያዎቹም አረምን አስተካክለን ብለው ያቀረቡት መሬት በፀሐይ ዙሪያ ለመዞር የሚፈጅባት ጊዜ የዩልዮስ ቄሣር አቈጣጠር እንደወሰነው ፫፻፷፭ -365? ቀኖችና ፮ -6? ሰዓቶች ሳይሆኑ ፫፻፷፭ -365? ቀኖች፣ ፭ -5? ሰዓቶች፣ ፵፰ -48? ደቂቃዎች፣ ፵፮ -46? ሰከንዶች ተደምረው በሚሰጡት ጊዜያት ነው በሚል ግምት ፍልስፍና በመራቀቅ ነው። በዚህም አባባላቸው የዮልዮስ ቄሣርንና የጎርጎርዮስን የዘመን አቆጣጠር ልዮነት ሰንጠረዥ ሠርተን በሒሳብ መልክ ስናየው

<u>፩. ፀሐይን በተመለከተ</u>

| | ቀኖች | ሰዓቶች | ደቂቃዎች | ሰከንዶች |
|---|---|---|---|---|
| የዮልዮስ ቄሣር | 365 | 5 | 59 | 60 |
| የጎርጎርዮስ | 365 | 5 | 48 | 46 |
| ልዩነት | 365 | 5 | 11 | 14 |

<u>፪. ጨረቃን በተመለከተ</u>

| | ቀኖች | ሰዓቶች | ደቂቃዎች | ሰከንዶች |
|---|---|---|---|---|
| የዮልዮስ ቄሣር | 29 | 12 | 44 | 25 |
| የጎርጎርዮስ | 29 | 12 | 44 | 3 |
| ልዩነት | 29 | 12 | 44 | 22 |

እንግዲህ ይህን ነው ማለትም በተለይ በፀሐይ ዓመት ተከሠተ ብሎ ያመነበትን የ□□ -11? ደቂቃና የ□□ -14? ሰከንድ ልዩነት ከ□□□□ -325? ዓ.ም የኒቃያ ጉባኤ ጀምሮ እስከ ፩፻፭፻፹፪ -1582? ዓ.ም ድረስ ለ ፩፪፻፶፯ -1257? ዓመታት ያህል አጠራቅሞ ፲ -10? ቀን አገኘሁ ሊልና በነዚህ ቀናት አማካኝነት ለራሱ ፍልስፍና እንዲመቸው ከማድረግ ጋር ወደ ፊት እንደምንገልጸው ከዓመቱ ላይ ዓመታትን’ ከቀኑ ላይ ቀናትን በመጨመር አንድነትን የሚያፋልስና የሚያናጋ ነገር ሊፈጥር የቻለውዐዐ

ለመጀመሪያ ጊዜ የፈጠረው አስደንጋጭ ነገርም ቢኖር ይህ የ ፲ -10? ቀን ልዩነት መረገዙ ሳይሰማ ማን እንደወለደውም ሳይታወቅ አድጎ ድንገት ብቅ ማለት ነውዐዐ ይኸውም እንዴት እንደታሰበ ማሰቢያውና መፈላሰፊያው ምን ዓይነት እንደሆነ ሊያስረዳ በማይችል ምክንያት ለምሳሌ ያህልም ሰዎች ጥቅምት 4 ቀን ማታ ተኝተው በማግስቱ ሲነቁ ጥቅምት ፭ -5? ቀን በመሆኑ ፋንታ ጥቅምት ፲፭ -15? ቀን ሆኖ እንዲያገኙት መደረጉ ነውዐዐ

በመሠረቱ እኛ ኢትዮጵያዊያን የዘመን መለወጫችንን መስከረም ፩ -1? ቀን የምናደርገው በቂ የሆኑ የእግዚአብሔር ቸርነቶችንና የተፈጥሮ ክሥተቶችን ምክንያት በማድረግ ነውዐዐ ለዚህም እኛ የመጀመሪያዎቹ እንዳልነበርን የባሕረ ሐሳቡ ታሪክ ያስረዳልዐዐ የተጀመረውም ቅድመ ክርስቶስ ፵፮ -46? ዓመት ሲሆን የጀመረውም ሮምን ይገዛ የነበረው ዮልዮስ ቄሣር ነውዐዐ እኛ ግን የተረከብነው ከመጀመሪያው ሶርያዊ ጳጳሳችን ማለትም ፍሬምናጦስ ከተባለው ከአቡነ ሰላማና ከዚያም በኋላ እየተፈራረቁ ይመጡልን የነበሩ ግብፃውያን ስለሆኑ ከሁለቱም ኦርቶዶክሳዊያን ክርስቲያን አገሮች ነውዐዐ

ይህንን ወር ለዚህ የዘመን መለወጫ ከአስመረጠው አንዱም አስቀድመን እነደጠቀስነው ወሩ ዲዮቅልጥያኖስ የተባለው አረመኔ ንጉሥ የክርስትና ሃይማኖታቸውን ጠልቶና ተመቅኝቶ ያስፈጃቸውንና የፈጣሪያቸው ክርስቶስን መስቀለ ሞት ተሸክመው የተከተሉት ክርስትያን ሰማዕታት የሚታሰቡበት ወር በመሆኑ በዚህ ምክንያት ነውዐዐ

ሌላው ደግሞ አሁንም የዚህን ወር ተፈላጊነት አጉልቶ የሚያሳየውና ከሌሎቹ ወር□ት የተለየ የሚያደርገው የራሱ የሆነ የአየር ጠባይ ባሕርይ ስላለው ነውዐዐ ይኸውም እንደ ኢተዮጵያ የክረምትና የበጋ’ እንደ አውሮፓውያን የበጋና የክረምት ማዕከላዊ መሸጋገሪያ እንደ መሆኑ መጠን ያለፉት ማለትም የሰኔ’ የሐምሌና የነሐሴ ወር□ት ክረምት ወይም በጋ የሆንበት የአየር ጠባይ ላለው አገር ሁሉ እንደ ክረምት ብርድና ቅዝቃዜ’ እንደ በጋ ፀሐይና ቃጠሎ የማይበዛበትና በሁሉም ነገር መካከለኛ የሚሆንበት’ መዓልቱ ከሌሊቱ’ ሌሊቱ ከመዓልቱ ካለመበላለጡና እኩል ከመሆኑ የተነሣ’ ቀኑ ለሥራ ሌሊቱ ለእንቅልፍ የተመጣጠነበት ድንቅ ወር ሆኖ በመገኘቱ ነውዐዐ

ከዚህም በስተቀር የዘመን መለወጫ ማለት እንደዚሁ ዘመን ከዘመን አየተለዋወጠ የዓለም ልደት የሚከብርበት’ ዕድሜው የሚረጠርበት’ ያለፈው ዓመት በተለያየ ምክንያት ለሕይወት ያልተመቸ ቢሆን አዲሱ ዓመት ግን የተሻለ ይሆናል ተብሎ ተስፋ የሚደረግበት’ የተመቸ ቢሆንም እንኳ ዕቅድ ከማውጣት ጋር ለበለጠ ኑሮ የሚመኙበት ተስፋውም እንደ ፍጹም ተስፋ ተረጥሮ እንኳንስ ሆኖ ገና ሳይሆን ደስታው የሚቀድምበትና የሚገለጽበት ማለት ከመሆኑም በላይ ከኢትዮጵያና ከመሳሰሉት አገሮች የአየር ጠባይ አንጻር በሃይማኖት ደረጃ ሲያዩት ሌላ ምሳሌያዊ ትርጉም ያለው ሆኖ ስለተገኘ ነውዐዐ

ይህንንም ኻዓለምና ታሪካዊ ህልውናው ከየት እስከየትኻ በሚለው በ□ኛው -2? አንቀጽና ከገጽ ፪ ጠ ፫ -2 ጠ 3? ባለው መሥመር ላይ በመጠኑም ቢሆን የዘረዘርነው ስለሆነ አሳጥረን አሁን በአጭሩ ስናየው የቅድመ መስከረም ክረምት የዘመነ ኦሪት፣ የድ□ረ መስከረም በጋ የዘመነ ወንጌል ምሳሌ እንደሆነ ነው የምንረዳው። እዚህ ላይ ይህ እንዴት ሊሆን ቻለ የሚል ጥያቄ ያለው ቢኖር ለዚህ የሚሰጠው መልስ

፩. የክረምት ወራት እንደሚታወቀው ሁሉ ሰማዩ በደመና መሬቱ በጉም ተሸፍኖ የሚጨልምበት፣ መብረቁ ድምፀ ነጎድጓዱ የሚያስደነግጥበት፣ ከዝናቡ አለማቋረጥ የተነሣ ጭቃው፣ ድጡ፣ ማጡ፣ ጎርፉና ማዕበሉ የሚያጥለቀልቅበት፣ ነፋሱ፣ ወጀቡና ውሽንፍሩ የቆመውን ነገር ሁሉ የሚያናውጥበትና የሚደረምስበት፣ ብርዱ ቆራው -ቅዝቃዜው? እጅና እግርን አሥሮ፣ ጅማቶችን አኮማትሮ የሚያንቀጠቅጥበት፣ ሰው ሁሉ በአብዛኛው ሁሉም ነገር አልቆበት፣ ኑሮውም ተወዶበት፣ አርሶ ዘርቶ ለአዲሱ ዓመት ከሚጠብቀው ተስፋ በቀር ለጊዜው ግን የሚራብበትና የሚቸገርበት ወራት እንደ ሆነ ሁሉ ዘመኑን ዘመነ ብሉይ፣ ዓመተ ኩነኔ -ዓመተ ፍዳ? ያሰኘው ይኸው ዘመነ ኦሪትም በሁሉም ነገር ሕይወታዊ የሥጋና የነፍስ ኑሮው በዘመነ ወንጌል ከሚጠበቀው ተስፋ በቀር የሞተበት፣ ፍትሕ ርትዕ ያልተቃናበት፣ ሕጉና ሥርዓቱ የከበደበት፣ መቅሠፍት ሥጋ በምድር፣ ኩነኔ ነፍስ በሰማይ፣ ከዚህም ሌላ የመሳሰለው ችግር ሁሉ እጅግ የጸናበት የጨለማ ዘመን ለመሆኑ፡

፪. የበጋ ወራት እንደሚታየው ሁሉ ደመናው ከሰማይ ተገፎለት፣ ጉሙ ከመሬት ተጠርጎለት፣ ከዚህም የተነሣ መላ ሌሊቱ በጨረቃና በከዋክብት፣ ቀኑ ደግሞ በፀሐይ ብርሃን አሸብርቆ፣ ሞቆና ደምቆ የሚታይበት፣ ዝናቡ፣ ብርዱና ቅዝቃዜው ቀንሶና ተመጣጥኖ መሬቱ ምጥጥ ብሎ ውሃው ጠርቶ የሚታይበት፣ ዕፅዋት፣ አትክልት፣ አዝርዕትና የመሳሰሉት፣ አረንጓዴ ስነ ፍጥረታት ሁሉ ለምልመው፣ አብበውና አፍርተው ሕሊናን ከሚመስጥ ድንቅነታቸው ጋር የሚመረቱበት፣ ልዩ ልዩ የሆኑ የቤትና የበረሃ እንስሳት አራዊት እንደየተፈጥሮ ዓይነታቸው ረብተው፣ ሰብተው የሚቦርቁበት፣ በዚህም ሁሉ የሰው ልጅ ከክረመበት ችግር ተላቆ ሕሊናውን በደስታ፣ ሕይወቱን በምግብ የሚያድስበት ወራት እንደሆነ ሁሉ፣

ዘመኑን ዘመነ ሐዲስ፣ ዘመነ ሥጋዌ፣ ዓመተ እግዚእ፣ ዓመተ ምሕረት ያሰኘው ሕገ ወንጌልም ቅዱስ ዳዊት አስቀድሞ ኻ የእግዚአብሔር ማዳን ለሚፈሩት ቅርብ ነው። ምሕረትና እውነት ጽድቅና ሰላም ተገናኙ እውነት ከምድር በቀለች ጽድቅም ከሰማይ ሆና ተመለከተች ኻ ሲል በመዝሙር ፹፬ ቍ ጠ ፲፫ -84÷ 9ጠ13?። እንደተነበየው፣ ቅዱስ ሉቃስም ኻ ክብር ለእግዚአብሔር በአርያም ይሁን ለሰው ነፃነቱ ይሰጠው ዘንድ በምድር ላይ ዕርቅ ተጀመረ እያለ በምዕራፍ ፪ ቍ ጠ ፲፬ -2÷ 10ጠ14? ተግባራዊነቱን እንደገለጸው አምላክ ሰው ሆኖ ዓለምን ለማዳን በገዛ ፈቃዱ የመጣበት፣ ፍትሕ ርትዕ የተገኘበት፣ ሕጉና ሥርዓቱ በንሥሐ ቅጣት ብቻ የቀለለበት ሕይወታዊ የብርሃን ዘመን ሆኖ ለመገኘቱ ዓይናችን በተጨባጭ የሚያየው ይኸው የተፈጥሮ ክስተት ማስረጃ ነው።

ለዚህም ነው ምሳሌያዊ አንጻርነቱን አይታ ትርጉማዊ ተስማሚነቱን ተመልክታ ስላገኘችው የኦርቶዶክስ ተዋሕዶ ቤተ ክርስቲያን ይህን የዘመን መለወጫ በዚህ ወር መጀመሪያ ላይ እንዲውልና በተመሳሳይነቱ እንዲከበር ያደረገችው።

# ኢትዮጵያዊያን ወገኖች ሆይ

እንግዲህ እስከዚህ ድረስ የታሪክ ምንጭ የሆነችውን ቤተ ክርስቲያንን ወክለን ከብዙ በጥቂቱ ከሙሉ በከፊሉ ስናቀርብላቸሁ የቀረውን ግን ባሕረ ሐሳብ -የዘመን መቁጠሪያ? ከተባለው የቤተ ክርስቲያን መጽሐፍ አንብባችሁ እንደምታውቁ ከመምህራን ጠይቃችሁ እንደምትረዱ ተስፋ እናደርጋለን።

ከዚህ በተረፈ ለዚህ ሙሉ ዓመት ያደረሰን አምላክ ከሀገራችን ሰላምና ነፃነት ከወገናችን ጤንነትና ደ ንነት ጋር ለሚመጣው ዓመት በሰላም እንዲያደርሰን አሜን በማለት ስንሰነባበት በማጠቃለያ መልክ የምናሳርገው ጸሎት ቢኖር ነቢየ እግዚአብሔር ኢሳይያስ በምዕራፍ ፷፩ ቍ ጠ ፩ -61 ቁ 1ጠ4? ላይ የጌታዬ የእግዚአብሔር መንፈሰ ረድኤት ለድሆች የምሥራችን እሰብክ ዘንድ፣ ልባቸው በ ዘን የተሰበረውንና የሚያለቅሱትን አጽናና ዘንድ፣ ምርኮኞችን ነፃ አወጣ ዘንድ፣ የታሠሩትን እፈታ ዘንድ ለቸርነቱ መግለጫ የተከላቸው የጽድቅ ዛፎች -የእውነት ሰዎች? እንዲባሉ፣ ለተመረጡት በመጠቃታቸውና በመዋረዳቸው ፋንታ የድል አክሊልን አቀዳጅ ዘንድ፣ በለቅሶ ፋንታ የደስታ ዘይትን እቀባ ዘንድ፣ በ ዘን መንፈስ ፋንታ የምስጋና ልብስን አጎናጽፍ ዘንድ፣ በዚህም ሁሉ የተወደደችውንና ፍትሕ ርትዕ-የሚዛናዊና የቀና ዳኝነት? የሚታይባትን የእግዚአብሔርን ዓመት፣ ፍርድ የሚሰጥባትን የቸርነቱንም ቀን አውጅ ዘንድ በረድኤት ቀብቶ ልኮኛል ሲል እነደተነበየው ሁሉ፣

አሁንም ይህን ይጠበቅ የነበረውን የ▯▯ -2000? ዓ.ም በነቢዩ ትንቢት መሠረት የእግዚአብሔር ረድኤትና ይቅርታ፣ ምሕረትና ቸርነት ተልኮ ሕዝብና መንግሥት፣ ሕዝብና ሕዝብ የሚታረቅበት፣ የታሠሩ የሚፈቱበት፣ ያዘኑ የሚጽናኑበት፣ የደኸዩ የሚበለጽጉበት፣ የተቸገሩ የሚረዱበት፣ የታመሙ የሚፈወሱበት፣ የተሰደዱ የሚመለሱበት፣ እነደ ዘመኑ ዓመታት መሙላት የጎደለው ሁሉ የሚሞላበት የጠመመው ሁሉ የሚቃናበት የሰላምና የፍቅር፣ የዕድሜና የጤና፣ የረድኤትና የበረከት፣ የዕቅድና የዓላማ፣ የልማትና የብልጽግና፣ የትምሕርትና የዕውቀት፣ የመሰማማትና የመደማመጥ፣ የመመካከር፣ ተስማምቶ የመወሰንና የመሥራት ዕድገት የሚገኝበት፣ ለሁሉም መሠረት የሆነውና ሰው ተወልዶ ሰው ሆኖ የሚታይበት ትዳራዊ ሕይወት አንቺ ትብሽ አንተ ትብስ በሚያሰኝ የመተዛዘን እሽቅድምድምና ለቤተሰብ ዓርአያ በሚሆን ተግባር አንድ በአንድ ጸንቶ የሚኖርበት፣ ከሁሉም በይበልጥ ይህን ሁሉ ተግባራዊ ለማድረግ አስፈጻሚ የሆነው ሕገ እግዚአብሔር በሃይማኖት ጽናት የሚጠበቅበት፣ ትዕዛዝ እግዚአብሔር በምግባረ ሰናይ ስፋት የሚከበርበት፣ ፈቃደ እግዚአብሔር በሥርዓት ጥበቃ የሚፈጸምበት በአጠቃላይም ይህንና ይህን በመሳሰለው መንፈሳዊ የሕይወት ኑሮ የሰው እኩልነት በእኩልነት የሚታይበት ዘመን ያድርግልን የሚለውን ምኞታዊ የተስፋ ልመና ከመማፀን ጋር በማቅረብ ይሆናል።

## አሜን።

## በስዊድን የኢትዮጵያ ኦርቶዶክስ ተዋሕዶ
## የደብረ ሰላም መድ▯ኔዓለም ቤተ ክርስቲያን

## <u>አዘጋጅ</u>

## ሊቀ ትጉሃን ጌጡ የኟላሸት